22100015

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1**

Thursday 13 May 2010 (afternoon)
Jeudi 13 mai 2010 (après-midi)
Jueves 13 de mayo de 2010 (tarde)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only. It is not compulsory for you to respond directly to the guiding questions provided. However, you may use them if you wish.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages. Le commentaire ne doit pas nécessairement répondre aux questions d'orientation fournies. Vous pouvez toutefois les utiliser si vous le désirez.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento. No es obligatorio responder directamente a las preguntas que se ofrecen a modo de guía. Sin embargo, puede usarlas si lo desea.




© International Baccalaureate Organization 2010

https://xtremepape.rs/

**ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየት ስጥ(ስጭ)፡፡**

**1.**

«ውይ! ውይ! ውይ! አንተ ደግሞ የማነህ ባለሙያ? እሰይ! እሰይ! እሰይ የእኔ ማር!» የማታውቃት ሴት ከኋላዋ መጥታ እቅፍ አድርጋ እየሳመች ማማሰያውን ተቀበለቻት፡፡ ተናደደች፡፡

«እዚህ ደግሞ ማን አመጣሽ በይ? ይህችን ልጅ ሳያስለክፏት አይቀሩም እናንተ?! አንቺ ባትለወጥ! አውቀሻት ነው እትዎይ?» ሌላዋ የፋንታነሽን እናት እየጠራችና ለሚስሟት ሴት ጥያቄዋን እያቀረበች ተጠጋቻት፡፡

«ኧረ አላወቅኳትም! አንቺዬ የማናት? ደሞ ደስ የምትል ነገር፡፡ የማነሽ ልጅ ዓለሜ?» አሏት

«ያባባ!» አለች፡፡ እያታለሉ ቢስሟትም ወጥ እንጨቱን ስለቀሟት ተናዳለች፡፡

«ውይ አፈር በበላሁ! የማናት አደራሽን?» ከፋንታነሽ ያጡትን አጥጋቢ መልስ ለማግኘት ወደ ሴትዮዋ አተኮሩ፡፡ እሷ ግን መልስ ከመስጠቷ በፊት ከት ብላ ሳቀችና፣

«አ...ዬ እትዎይ! ሙሽራዋ እኮ ናት! የሷን ሰርግ ልትበይ አይደለም እንዴ ጋራ ዙረሽ መጥተሽ ጉድ ጉድ የምትይው?»

«ኧረግ በሞትኩት! የመኳንንት ልጅ ይህች ናት? እኔኮ ከአሁን አሁን ከድስቱ ተተክታችሁልኝ ሄጀ ባየኋት እያልኩ ነበር፡፡ አ...ይ...ኧረ ይችንስ መዳር በፍጡር መጫወት ነው አደራሽን!?»

«አ...ይ! አንቺ ደግሞ! ከታበባ ልጅ አንሳ ነው? ከሶስት ወር በኋላ እኮ ስድስት ዓመት ይሞላታል፡፡»

«እንዴት እየሄደላችሁ ነው እናንተ ሰዎች?» የፋንታነሽ እናት ብክን ብክን እያለች መጣች፡፡ የሥራው ብዛት እንቅልፍ ነስቷት ስለሰነበተ ግርጥት ብላ በሽተኛ መስላለች፡፡ ፋንታነሽ ተደብቃ መምጣቷ ትዝ ያላት እናቷ ስትመጣ ነው፡፡ ደነገጠች፡፡

«አዬ ባትለወ...ጥ እንደው ይህችማ ገና አንድ ፍሬ አይደለች አደራሽን?!»

«ኧረ እሱን ተውትና ይልቅ ሙሽራዋን በየቦታው እያንከለከላችሁ እንዳታስለክፏት፡፡ አሁን እኮ ከዚህ ወጡ መሃል መጥታ ነው ያገኜናት፡፡»

«ውሃው በላኝ እኮ አንችዬ! ምን አባቴ ላርጋት?» አለች የፋንታነሽ እናት ስለ ልጇ እንደሚያወገም ሆነ ልጇ በመሃላቸው ስለመኖሯ የተረዳችው ዘግይታ ነው፡፡

«አይ! ጥሩ አይደለም ከዛው ተቆጥተሽ አስቀምጫት፡፡ የቄብ ልጅ በፊት ማን ባየልኝ በኋላ ማን አየብኝ አሉ፡፡ ከሆነ በኋላ ወየው! ወየው! አይጠቅምም፡፡»

«ኧረ የማደርጋት ጠፍቶኝ እንጂ ቸል ብያትስ አይደለም አንችዬ፡፡ ልጆቹን ሁሉ አሰባስቢ የምትፈልገውን አሟልቼ ተቀመጭ አልኩ፡፡ መቸ በጅ የምትል ሆነች፡፡ ይህን ትልቅ ጉዳይ ወና ትቼ አቅፌአት አልቀመጥ፣ ግራ ገባኝ እኮ!? እስቲ ነይ ወዲህ አንቺ!



https://xtremepape.rs/

ኧረ ምኒቱ ነሽ አያ! እንግዲህ እንቢ ካልሽ እሱን ቀሚስ ነው የማስወልቅሽ!» የፋንታነሽ እናት የክፉው ነገር ማስጠንቀቂያ ሰውነቷም እያንቀጠቀጣት ነበር የምትናገረው፡፡

ፋንታነሽ የለበሰችትን አዲስ ቀሚስ እንዳታወልቅባት ስብስብ አድርጋ በማቀፍ ለመከላከል ሞከረች፡፡ ይህችን አረንጓዴ አዲስ ሽብሽቦ ዛሬ ጠዋት ነው የለበሰቻት፡፡ ሆኖም ቀሚሱን ስትሰበስበው አተር ከምታክል ሆዷ ጀምሮ ወደታች ያለው አካሏ ተራቆተ፡፡

«ኧረ እባክሽ ዝቅ አድርጊው ከዚህ እሳት ላይ ምች ይመታሻል! ኧረ እንደው ይቺን የሰጡ እዳ!» እናቷ እየተማረረች ቀሚሱን አስለቅቃ ሸፈነቻት፡፡

«ኧረ እንደው ጥፋት ነው የሰራችሁት እቴ! በአጅሬ ልጅ ማቅለጥ እንዴትስ ነው ተለይታ የምትሰነብተው?» ሴትዮዋ አሁንም ስጋታቸውን አከሉ፡፡ የፋንታነሽ አባት የወንድማቸው ልጅ ቢሆንም ከቤቱ የሚመጡት እንዲህ ሰርግና ትላልቅ ድግስ ሲኖር ነው፡፡

«ኧረ እኔ ምን አውቄ እቴ! ያው ከሰው አማጋ ስታንቋርር መሰንበቷ ነው እንጅ፣ አንድም የእሷ ነገር ነው አቅል ነስቶኝ የሰነበተው፡፡»

«ለመሆኑ ለአላማጅነት አብሯት የሚሄደውስ ማነው?»

«ያው ወንድሟ ነዋ! ሌላማ ማንን ትቀርባለች፡፡ እሱም ጥሎባት ትወደዋለች እንጂ ልጅ ማታለል አይችልበት! እንደ አባቱ ገጨሽኝ ቢጤ ነው፡፡» አለች አባቱ ለልጆች መጥፎ አባት ባይባልም ለእሷ የማይመች ባህሪ እንዳለው እግረ መንገዷን ልትጠቁማቸው፡፡

«ኧረ ደግም አልሰራችሁ እቴ! ባይሆን የዘንድሮን ማክረም ነበረባችሁ፡፡»

«ወይጉድ! ያልደረሰበት ሰው፡፡ ዘንድሮ ካልሆነ ሙተን እንገኛለን ብለው ካፍንጫችን ላይ ቆሙ! የመጀመሪያ ልጃችን ነው፡፡ ትልቅ ሰርግ ለማድረግ የዘንድሮ አዝመራ እንዲያመልጠን አንፈልግም ይላሉ፡፡»

«ኤዬ! 'ቅቤ ነጋዴ ድርቅ ያወራል' አሉ፡፡ ከርሞ አዝመራ የለም ተብለዋል፡፡ ካልፈለጉ ይተውታ! የመኳንንት ልጅ ባል እንዳላጣች ነው?» አሉ ሴትዮዋ የወንድማቸውን ልጅ ዘረ ጭዋነትና የሞላ ሃብት እያሰቡ፡፡

«እሱስ ግቢውን እኛም ወደነዋል፡፡ እንደሚያውቁት ሰዎቹ ዘረ ጭዋዎች ናቸው፡፡ በዚህ ላይ ልጁም መጠቅጠቂያ ነው አልኩም! ከቁመቱ፣ ከውፍረቱ፣»

**እንየ ሽበሽ፣ «የሰርጉ መልስ»፣ ያልተናበቡ ልቦች፣2000፡፡**

– የህፃንዋ ገፀባህሪ አሳሳልና ችግርዋ ላይ አስተያየት ስጥ፡፡

– ደራሲው በጽሁፉ ውስጥ የሚገኘውን ዋነኛ ጉዳይ እንደምን አቀረበው?

– በጽሁፉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንደምን እንደቀረቡ አስተያየት ስጥ፡፡

– ጸሃፊው ሊያስተላልፍ የቻለው መልእክት ምንድነው?



https://xtremepape.rs/

**2.**

# ጦስ ጥንቡሳስ

ልጅ፡-
ድሮ ድሮ እናት
ልጅ ሲታመምባት
 እሱ እንዲድንላት፤
በሽታው እንዲጋባባት
ጦስ ጥንቡሳሱን ወስዳ
 በተንጋለለበት፤
ሦስቴ ዞራው ድፍት...
ሦስቴ ዞራው ድፍት...
አሁንም ዞራው ድ ፍ ት
 በማለት እስከምን ድረስ
 ልጇን እንደምትወድ ታሳይ ነበረ።
**ልጅ፡-** ባንተ ባሰ...
ጥንት የተረሳውን
ይህን ዛሬ ደገምክ
አደረክ-አደረክ፤
ልጅ ዐዋቂ ሳትል
የሁላችንንም
ጦስ ጥንቡሳስ ወሰድክ!
 **ልጅ፡-**
 ልብህ ብርሃን
 ልብስህ ብርሃን
 ጥርስህ ብርሃን
 ግጥምህ ብርሃን
 ዜማህ ብርሃን
ዝናር-ፈገግታህ-ጨለማህ-ብርሃን
ቁጣና ግሣጼህ ሁለንተናህ ብርሃን
ልጅ ማነህ? አንተ ማንስ ልበልህ ማን?
 ትከሻህ ላይ እሳት
 ደረትህ ላይ መብራት
 ገጽታህ ላይ ኩራት
 እልብህ ውስጥ ፀዳል
ካይንህ ዕምብርት ብርሃን
ሐኖስ ነህ ወይ ጠፈር መካከለ እሳት
 (እሳተ መለኰት)
ኀልፈት የሌለብህ ውላጤ የለበት
 ዙርያ ገባህ ገነት (አትክልት)
ይባቤህ ዝማሬህ፣ መንግሥተ ሰማያት።
 ዲያብሎስ በጥርሱ-በጥርሳ ጥርሶቹ
 እየሰረሰረ፣
እየስቀሰቀ-እየፈላለጠ-እየቆረጠመ፣
 ያልቻለህ ለመግደል
 ያልቻለህ ለማጥፋት።



https://xtremepape.rs/

ልጄ!
ድሮ ድሮ እናት
ልጅ ሲታመምባት
    እሱ እንዲድንላት፣
በሽታው እንዲጋባባት
ጦስ ጥንቡሳሱን ወስዳ
    በተንጋለለበት፤
ሦስቴ ዞራው ድፍት...
ሦስቴ ዞራው ድፍት...
አሁንም ዞራው ድ-ፍ-ት
    በማለት እስከምን ድረስ
    ልጇን እንደምትወድ ታሳይ ነበረ::
**ልጄ**፡- ባንተ ባሰ...
ጥንት የተረሳውን
ይህን ዛሬ ደገምክ
አደረክ-አደረክ፤
ልጅ ዐዋቂ ሳትል
የሁላችንንም
ጦስ ጥንቡሳስ ወሰድክ!

**አብርሃም ረታ፣ «ጦስ ጥንቡሣስ»፣ እችክ እችክ፣2000::**

– የወጣቱ ገፀባህሪ ሰብእና እንደምን ቀረበ?

– በገጣሚው ቋንቋ በተለይም በቃላት አመራረጡና በምሰላው ላይ አስተያየት ስጥ፤ የቃላት አመራረጡ በአንባቢው ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖም ግለጽ::

– የግጥሙ ቅርጽ ግጥሙን ለመረዳት የሚኖረው አስተዋጽኦ ላይ አስተያየት ስጥ?

– ግጥሙ በተለየ ያሳደረብህ ስሜት ምንድነው?



https://xtremepape.rs/